የብርሃን ባንክ አ.ማ. መመሥረቻ ጽሁፍ/ሰነድ/

እኛ የብርሃን ባንክ ኢ.ማ ባለአክሲዮኖች በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) እና በኢፌዲሪ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 400(1)መሠረት ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም ባደረግነው ስድስተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከአሁን ቀደም የነበረውን የባንኩን/የማህበሩን/ መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በአንድ በማጠቃለል በዚህ የተሻሻለ **"መመስረቻ ጽሁፍ"** እንዲተካ አጽድቀናል፡፡

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 1. የማህበሩ ስም

የማህበሩ ስም ብርሃን ባንክ አ.ማ. ይሆናል፡፡

አንቀጽ 2 የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ

1. የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/05(ወረዳ 5) የቤት ቁጥር አዲስ ይሆናል፡፡
2. ማህበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ በማናቸውም ቦታ እንደአስፈላጊነቱም አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋም/ሊከፍት/ ይችላል፡፡

አንቀጽ 3 የማህበሩ የሥራ ዓላማዎች

የማህበሩ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ልዩ ልዩ ዓይነት ተቀማጭ የአደራ ገንዘቦችን በማሰባሰብ አስፈላጊና ውጤታማ ለሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሥራዎች ያውላል፡፡
2. የውጭ ምንዛሪን መግዛት፤ መሸጥና መያዝ ፤ የውጭ ምንዛሪ ሥራንና ሌሎች ከውጭ ምንዛሪ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ማከናወን፤ እንዲሁም በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር ይገዛል ይሸጣል፡፡
3. በገንዘብ ማስከፈያ ፤ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች የዕዳ ማረጋገጫ ሰነዶች አማካኝነት በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ ሥራ ይሠራል፡፡
4. ሲጠየቁ የሚከፈሉ የቁጠባ ሒሳቦችን እና ሌሎች ለተወሰነ ጊዜ በአደራ የሚቀመጡ ሒሳቦችን መቀበል፤

5. የባንኩን የብድር ፖሊሲ ለሚያሟሉ የግል ሽርክና ድርጅቶች እንዲሁም መንግስታዊ ተቋማት የተለያዩ ብድሮችን ፤ የቅድሚያ ብድሮችን እና ከተቀመጠው ገንዘብ በላይ የሚደረግ ወጪን(ኦቨር ድራፍት) መፍቀድና አገልግሎቶችን መስጠት፡፡
6. ለግል ነጋዴዎች እና በቅይጥ የንግድ ሥራ ድርጅቶች (ኢንተርፕራይዝ) ውስጥ ለሚገኝ የግሉ ክፍል የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን ለሽያጭ ማቅረብ፤
7. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በሚሰጥ ፈቃድ መሰረት ስለማናቸውም ንብረት ድልደላና ክፍፍል አንድ አስፈጻሚ ባለአደራ ወይም ባንክ የሚያከናውናቸውን መደበኛ ተግባራት ማከናወን፡፡
8. የኢትዮጵያ መንግስት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች (ኔጎሽየብል ሴኪዩሪቲስ) የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ቦታና መሬት እንዲሁም ሌሎች በመያዣነት የሚሰጡ ንብረቶች ወይም ባንኩ ለሰጣቸው ብድሮች ቅድመ ብድሮች ወይም ኦቨር ድራፍቶች በዋስትና / በመያዣነት የተሰጡ ሆነው በስምምነቱ መሰረት ዕዳው በወቅቱ ተከፍሎ ለባለንብረቱ ያልተመለሱትን ሁሉ መያዝ መግዛትና መሸጥ፡፡
9. የዋስትና ሰነዶችን ዕንቁዎችን የከበሩ ድንጋዮች ዋጋ ያላቸው ንብረቶችን ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና ድንጋጌ መሰረት ተቀብሎ በአደራ በካዝናዎች ማስቀመጥ፡፡
10. አክስዮኖችን፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በገንዘብ የሚለወጡ ሠነዶችን እና የግዴታ ሠነዶችን ለማውጣት መደራደር ዋስትና መስጠት እና ማስተዳደር፡፡
11. በራሱ ስምና በራሱ ገንዘብ ትርፋማ በሆኑ የንግድ ድርጀቶች ውስጥ አክስዮኖችን መግዛት እነዚህኑም አክስዮኖች እንደአስፈላጊነቱ መሸጥ፤
12. ለደንበኞች የወኪልነት አገልግሎት መስጠት እና በዚህም ሚናው የገንዘብ የዋስትና ሠነዶች ግዥና ሽያጭ ሥራዎች ማከናወን፡፡
13. ዋስትና ባለበት ወይም በሌለበት አኳኋን የዋስትና ወይም የተያዥነት ውሎችን መፈራረም፡፡
14. ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ለመኖሪያና ለንግድ ሥራ የሚሆኑ ቤቶችን መግዛት መንከባከብ እና መሸጥ፤
15. ሥራውን ለማካሔድ ገንዘብ መበደር፤ ለተበደረውም ገንዘብ ንብረቶቹን በዋስትና ለማስያዝ ለአበዳሪዎቹ ግዴታ መግባት ወይም ለአበዳሪዎቹ ማስተላለፍ፤
16. የሚተላለፉ የምንዛሪ ወረቀቶችን የክፍያ ትዕዛዞችንና የተስፋ ሰነዶችን በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ ማውጣት መቀበል መቀነስ መግዛትና መሸጥ፡፡
17. ለአስተማማኝ የባንክ የንግድ ጠቃሚ በሆኑና ከዚህ በላይ ተለይተው ባልተዘረዘሩ በማናቸውም ግብይቶችና ሥራዎች ሁሉ መካፈል፡፡
18. በአጠቃላይ በሕጉ መሰረት ሁሉም ዓይነት የንግድ ሥራዎች፤ ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተመሳሳይ ወይም ተዛማጅነት ያላቸውንና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ሌሎችንም የባንኩን ዓላማዎች የሚያራምዱትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 4 የማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)

1. የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል) **ብር** 3,450,094,000.00 (ሦስት ቢሊየን አራት መቶ ሃምሳ ሚሊየን ዘጠና አራት ሺ)ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 3,450,094,000.00 (ሦስት ቢሊየን አራት መቶ ሃምሳ ሚሊየን ዘጠና አራት ሺ) ተከፍሏል፡፡
2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ዋና ገንዘብ የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) በሆኑ ብዛት 3,450,094(ሦስት ሚሊየን አራት መቶ ሃምሳ ሺ ዘጠና አራት) መደበኛ አክሲዮኖች ተከፋፍሏል፡፡
3. የማህበሩ ዋና ገንዘብ መጨመር ካፒታል ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 52-55 እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 442 እና በተከታዮቹ እንዲሁም በአንቀጽ 462 እና በተከታዮቹ መሠረት እንደ አግባቡ ይፈጸማል፡፡

አንቀጽ 5፡ <u>የማህበሩ እና የባለአክስዮኖች ኃላፊነት</u>

1. የማህበሩ ኃላፊነት ባለው ሀብት መጠን የተወሰነ ይሆናል፡፡
2. አግባብነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ በመክፈልና በማህበሩ ውስጥ ባላቸው አክስዮን መጠን የተወሰነ ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ስለ አክስዮን፣ የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

አንቀጽ 6፡ <u>የማህበሩ አክሲዮኖች</u>

1. ማህበሩ የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) የሆነ መደበኛ አክስዮኖች ተብለው የሚመዘገቡና የተወሰነ ዋጋ የሚኖራቸው አንድ ዓይነት አክስዮኖች ይኖሩታል፡፡
2. የማህበሩ ባለአክሲዮን መሆን ስለሚችሉ ሰዎች እና አንድ ሰው መያዝ ስለሚችለው ከፍተኛው የአክሲዮን መጠን በባንክ ስራ አዋጅ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. አንድ ባለአክስዮን በማህበሩ ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባው አነስተኛ የአክስዮን ብዛት የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 7፡ <u>የባለአክሲዮኖች መብት</u>

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው.) እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እንደዚሁም ሌሎች በየጊዜው የሚወጡ የባንክ ስራ እና የባለአክሲዮኖች መብቶች የሚመለከቱ ሕጎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ከዚህ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል።

1. በማህበሩባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የመካፈል መብት፤
2. በባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወሰነው መሰረት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከሚገኘው የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ በሕግ ለተደነገጉት ሕጋዊ ተቀማጭ ገንዘቦች እና ግዴታዎች የሚውለው ከተቀነሰ በኋላ ከተጣራው ትርፍ የመካፈል መብት፤
3. እያንዳንዱ ባለአክስዮን ባዋጣው ካፒታል መጠን የሚሰላ ሆኖ ማህበሩ ፈርሶ ሥራ በሚያቆምበት ጊዜ ከንብረቱ ሽያጭ ከሚገኘው የተጣራ ገቢ ድርሻውን የማግኘት መብት፤
4. እያንዳንዱ አክስዮን እኩል አንድ ድምፅ የያዘ ሆኖ በያዘው የአክስዮን ብዛት ልክ ድምፅ የመስጠት መብት፤
5. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7(4) ላይ የተጠቀሰው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በሚያወጣው መመሪያ በማናቸውም የባለአክስዮኖች ጉባኤ ላይ በውክልና ወይም በማህበሩ ተበዳሪዎች የሚሰጥ ድምጽ ላይ ገደብ ሊያደርግ ይችላል።
6. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 381 ላይ በተደነገገው መሰረት ቃለጉባኤዎችን እና ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ የተገኙ አባላትን ዝርዝር የመመልከት መብት እና የሒሳብ ሚዛንና እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ፤የዳይሬክተሮች ቦርድና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎችና ሌሎች ሰነዶችን የመውሰድ መብት፤
7. ካፒታሉ እንዲጨምር ለማድረግ ሲባል አዲስ የሚወጡትን አክስዮኖች /በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አክስዮኖችን በያዘው/ በያዘችው አክስዮኖች መጠን ድርሻ ላይ ተመስርቶ ለመግዛት የቀደምትነት መብት።
8. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ተደርጎ በቀረበ ጉዳይ ላይ ከድምዳሜ ለመድረስ የሚያስፈልግ ተጨማሪ መረጃ ለጉባኤው እንዲቀርብ የመጠየቅ መብት፤
9. የአክስዮን ድርሻውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሸጥ፤ በስጦታ የመስጠት ወይም በ3ኛ ወገኖች ዘንድ በዋስትና የማስያዝ መብት አለው።
10. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ የመመረጥ ወይም ሌሎችን የመምረጥ መብት አለው።
11. በሕግ የተቀመጡ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም ባለአክስዮን እራሱ ሳይስማማ የአባልነት መብቶቹን ሊነፈግ አይችልም።

አንቀጽ 8 የባለአክስዮኖች ግዴታና ተጠያቂነት

1. የማህበሩ ባለአክስዮኖች ተግባሮች፤ ግዴታዎችና ተጠያቂነት አግባብነት ባላቸው የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008(በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው)፤ እና በተጠቀሱት አዋጆች መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ ይሆናሉ።
2. ማናቸውም ባለአክስዮን ለመክፈል ግዴታ የገባበትን ወይም የፈረመውን የአክስዮን ዋጋ እንዲያስገባ ሲጠየቅ የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 9 ክፍያ ያልተፈጸመባቸው አክስዮኖችን በሚመለከት የሚደረግ ጥሪ

1. የአክስዮኖቹ ባለይዞታዎች የቀድሞ አስተላላፊዎች እና ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ለአክስዮኑ ዋጋ ክፍያ በአንድነትና በተናጥል ኃላፊ ናቸው።
2. አክስዮኖቹ የተሰጡት በአለባ ጥቅም እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለ የአክስዮን ገንዘብ ጥሪው መሰረት ቀሪውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።
3. ማናቸውም ለመግዛት የፈረመ ሰው ወይም ባለአክስዮን የሆነ ሰው የራሱ የሆነውን አክስዮን ያስተላለፈ እንደሆነ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ገና ላልተከፈለው ገንዘብ ኃላፊነት የለበትም።
4. ቀሪውን ያልተከፈለ የአክስዮን ገንዘብ በተወሰነው ቀን ያልከፈለ ባለአክስዮን ላይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 289 ንዑስ አንቀጾች 3-7 የተደነገጉት ተፈጻሚነት አላቸው።

አንቀጽ 10. የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. ማህበሩ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 274(2) መሰረት የባለአክስዮኖችን ስም፣አድራሻ፣ ዜግነት፣ አክስዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፤ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን፤ ባለአክስዮኖቹ በባለአክስዮንነት የተመዘገቡበትን ቀን ያካተተ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ማዘጋጀትና በዋናው መ/ቤት መያዝ አለበት። መዝገቡ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል።
2. ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ፈቃድ ያለው ማንኛውም አካል በማህበሩ ዋና መ/ቤት ወይም በዋና የስራ ቦታው ላይ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ወቅት መዝገቡን በግልፅ ለመመርመር ይችላል።

አንቀጽ 11. የአክሲዮን ዝውውር

1. የአክስዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በሥራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ሳይቃረን ያለምንም ገደብ ሊዘዋወር ወይም ሊተላለፍ ይችላሉ።

2. ማንኛውም የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በጽሑፍ መስፈርትና የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያፀድቀው ፎርም መሠረት መሆን አለበት።
3. ማንኛውም የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፍ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ መመዝገብ ያለበት ሲሆን በመዝገቡ ውስጥ እስካልሰፈረ ድረስ ውጤት አይኖረውም።
4. ማንኛውም ባለአክስዮን ሕይወቱ በሚያልፍበት ጊዜ ሕጋዊ ወራሾቹ በባለአክስዮኑ ፈንታ የሚተኩ ይሆናል።
5. ከአክስዮን ዝውውር ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመተካት ለባንኩ ሊከፈሉ የሚገቡ የአገልግሎት ክፍያዎች የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ 12 የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ

1. የማህበሩ ዓመታዊ ትርፍ ለባለአክስዮኖች የሚከፋፈለው ለትርፍ ክፍያው መከፈል ምክንያት በሆነው በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ወቅት ባላቸው የተከፈለ አክስዮን ይዞታ መጠን የተከፈለበትን ቀን ታሳቢ በማድረግ ነው።
2. ከተጣራ ትርፍ ላይ የትርፍ ድርሻ ክፍያ የሚደረገው ማንኛውም ግብር፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሒሳብና ጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚያጸድቃቸው የዚሁ ዓይነት መጠባበቂያ ሒሳቦች ከተቀነሱ በኋላ ነው። በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ቀሪው ገንዘብ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 12(1) መሰረት ይከፋፈላል።
3. የትርፍ አከፋፈል የማህበሩ ኦዲተሮች በመረመሩትና የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ባፀደቀው የተጣራ ትርፍ ድምር ላይ በመመስረት ተፈጻሚ ይሆናል።
4. ለክፍፍል የሚሆነው የተጣራ ትርፍ ከሒሳብ ዓመቱ ትርፍ ላይ ያለፈው ዓመት ኪሣራዎችና ማናቸውም የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያዎች (ለዳይሬክተሮች ቦርድና ለሌሎችም አካላት የተፈቀዱ ወጪዎችና ክፍያዎች) ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ነው።
5. ተቀባይነት ካገኘው የሒሳብ ሚዛን ውጪ የሚደረግ የትርፍ ድርሻ ክፍያ እንደጉድለት ተወስዶ በሕግ ያስቀጣል።
6. የትርፍ ክፍያው ቀንና ዝርዝር ሁኔታዎች በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።

ምዕራፍ ሦስት

የማህበሩ አስተዳደር አካላት

አንቀጽ 13 የማህበሩ አስተዳደር አካላት

1. የማህበሩ የአስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የባለአክስዮኖች ጉባኤ

ለ. የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሐ. ዋና ሥራ አስፈጻሚ

መ. የማኅበር ጸሃፊ

ሠ. የውጭ ኦዲተር /ኦዲተሮች

2. ከዚህ በላይ የተመለከቱት የማህበሩ የአስተዳደር አካላት ሥልጣን፤ ተግባርና ኃላፊነት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች እንዲሁም በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሰረት ይሆናል፡፡

ምዕራፍ አራት
የማህበሩ ባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

አንቀጽ 14፡ <u>ጠቅላላ ደንቦች</u>

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም ባለአክሲዮኖች ሊሳተፉ የሚችሉበት የማህበሩ የበላይና ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ሲሆን የባንኩን ተግባራት በበላይነት ለመምራት ሙሉ ስልጣን አለው፡፡
2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው በአካል በመገኘት ወይም አስተማማኝ በሆነ ኤሌክሮኒክ ዘዴ ሊደረግ ይችላል፡፡ አስተማማኝ የሆነ ኤሌክሮኒክ ዘዴ የሚባለው የተሰብሳቢዎችን ማንነት መለየት፣ ተሰብሳቢዎች በአንድ ጊዜ መሳተፍ፣ ድምጽና ምስል ሳይቆራረጥ ማስተላለፍ፣ በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ አስተያየትና ድምጽ መስጠት እና የሚሰጠው ድምጽ መቁጠር የሚያስችል ሲሆን ነው፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በፅሑፍ ወይም ማንነታቸውን ለመለየት በሚያስችል ኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለፅ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

<u>አንቀጽ 15 የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣን</u>

1. የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ የበላይ አካል ሆኖ የራሱን ተግባራት የመምራት ሥልጣን ያለው ከፍተኛው የማህበሩ ባለሥልጣን ነው፡፡ ይህ አጠቃላይ ሀሳብ በምንም ዓይነት ሳይቀነስ ማህበሩ የሚያካሒደውን የንግድ ሥራ በሚገዛው ሕግ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 17 እና 18 የተጠቀሱት ሥልጣኖች አሉት፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቶ እና አስፈላጊው የድምጽ ብልጫ አግኝተው የሚተላለፉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በስብሰባው ያልተካፈሉ፣ ድምጸ ተአቅቦ ባደረጉ፣ በሃሳብ በተለዩ፣ ድምጽ ለመስጠት ችሎታ የሌላቸው ወይም ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ ባለአክሲዮኖች ጨምሮ በሁሉም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 16 ልዩ ልዩ ዓይነት ጉባኤዎችና የጉባኤው ጥሪ

1. ጠቅላላ ጉባኤዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ናቸው፡፡
2. መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኦዲተሮች ጠሪነት ሊደረግ ይችላል፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወይም በኦዲተሮች ሲጠራ ወይም ቢያንስ ከማህበሩ ካፒታል/ዋና ገንዘብ/ 10% የሆነውን የሚወክሉ ባአክስዮኖች ሲጠይቁ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡
4. እንደዚሁም ጠቅላላ ጉባኤዎች እንደሁኔታው በብሔራዊ ባንክ ወይም በሂሳብ አጣሪዎች ወይም በፍ/ቤት ሹም ሊጠሩ ይችላሉ፡፡
5. የባለአክስዮኖች ጉባኤ የሚመራው በዳሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፤ እሱ በማይኖርበት ጊዜ በዳሬክተሮች ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ስብሰባው የተጠራው በኦዲተሮች ፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በሒሳብ አጣሪ ከሆነ ስብሰባውን በጠራው አካል ይመራል፡፡

አንቀጽ 17፡ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

1. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በየአመቱ እያንዳንዱ የሂሳብ አመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ይደረጋል፡፡
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፤ አግብብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎችና በሥራ ላይ ባሉት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተጠቀሱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

3.1 የማህበሩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ፣ የዳይሬክተሮችና የኦዲተሮች ሪፖርቶች በመመርመር እንዲጸድቁ ወይም እንዲሻሻሉ ወይም ውድቅ እንዲሆኑ ይወስናል፡፡

3.2 በትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ይወስናል፡፡

3.3 የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ ለመሾም የሚያስችል ፖሊስና የምርጫ አፈጻጸም ሥነሥርዓት ደንብን/መመሪያን ያወጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ያሻሽላል፡፡

3.4 አግባብነት ባለው ሕግ ወይም ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት በጉባኤው ዕለት ለሚከናወነው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን የሚያስፈጽሙ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ከባለአክስዮኖች መካከል ይመርጣል፡፡

3.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፤ የስራ ዋጋቸውን ይወስናል፡፡

3.6 የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፤ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜያቸውንና የስራ ዋጋቸውን ይወስናል፡፡

3.7 ማህበሩ የግዴታ ወረቀቶችን እንዲያወጣ መፍቀድና ከዚያም ጋር በተያያዘ የሚሰጡትን መያዣዎች ይወስናል።

3.8 ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከተመደቡት ጉዳዮች በቀር በሌሎች የማህበሩ ጉዳዮች ሁሉ ይወስናል።

አንቀጽ 18፡ <u>አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ</u>

1. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።
2. ሌሎች በሕግ ተለይተው የተሰጡ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
    - 1.1 የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ማጽደቅ፤ ማሻሻል፤
    - 1.2 የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ ወይም መቀነስ፤
    - 1.3 የማህበሩን ዜግነት መለወጥ፤
    - 1.4 ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ዓላማዎቹ እንዲለወጡ፣ ወደ ሌላ አይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም ከሌላ ማህበር ጋር እንዲዋሃድ መወሰን፤

አንቀጽ 19፡ <u>ምልዓተ ጉባኤ እና የድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም የማህበሩ ጉባኤ ውሳኔ ማሳለፍ የሚችለው ምልዓተ ጉባኤው የተሟላ ሲሆንና በጉባኤው በተገኙት ባለአክሲዮኖች የአብላጫውን የድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው።
2. ምልዓተ ጉባኤ የሚታሰበው ድምጽ የመስጠት መብት የሌላቸው አክሲዮኖች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪዎቹ አክሲዮኖች በማህበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ ባላቸው ድርሻ መሰረት ነው።
3. ለድምጽ በብልጫ አቆጣጠር ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተፃፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም።
4. ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቶ እና አስፈላጊው የድምጽ ብልጫ አግኝተው የሚተላለፉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በስብሰባው ያልተካፈሉ፣ ድምጸ ተአቅቦ ያደረጉ፣ በሃሳብ በተለዩ፣ ችሎታ የሌላቸው ወይም ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ ባለአክሲዮኖች ጨምሮ በሁሉም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

5. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ በቀላል አብላጫ ድምፅ ላይ ተመስርቶ ውሳኔዎችን መመርመርና ማሳለፍ አለበት፡: ይህም የሚሆነው፡-

   ሀ. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ የሚወክሉ ባለአክስዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ፤ ወይም

   ለ. በመጀመሪያው ጥሪ ላይ ምልዓተ ጉባኤ ካልተገኘ በ2ኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል)ግምት ውስጥ ሳይገባ ፤

6. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው

ሀ. በመጀመሪያው ጥሪ ከ1/3ኛ ያላነሱ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው የሁሉም አክስዮኖች ባለቤቶች ሲገኙ፡ ወይም በእንደራሴ ሲወከሉ።

ለ. በሁለተኛው ጥሪ ከ1/4ኛ ያላነሱ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው የሁሉም አክስዮኖች ባለቤቶች ሲገኙ ወይም በእንደራሴ ሲወከሉ፤

ሐ. በሦስተኛው ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክስዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለአክስዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ ነው።

7. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የጸና የሚሆነው በጉባኤው የተገኙት ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክስዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን በሚወክሉት ድምፅ ከተደገፈ ነው።
8. አስቸኳይ ጉባኤው የማህበሩን/የባንኩን/ ዜግነት መለወጥ የሚችለው ወይም በነባር አክስዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ የሚችለው ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸውን ባለአክስዮኖች ሙሉ ድጋፍ ያገኘ እንደሆነ ነው።
9. ሕግን ፤ የማህበሩን መመሥረቻ ሠነድን በመከተል የተደረጉት የስብሰባው ውሳኔዎች በስብሰባው ያልተገኙትን ወይም በሃሳብ ያልተስማሙትን አባላት ጨምሮ ሁሉንም ያስገድዳል።

አንቀጽ 20 የጠቅላላ ጉባኤዎች የማስታወቂያ ጊዜ

1. ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች የሚደረግ ጥሪ ስብሰባው እንዲደረግ ከተመረጠበት ቀን ቢያንስ ሃያ አራት ቀናት አስቀድሞ በሃገራችን ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባላው ጋዜጣና በማህበሩ ድረ ገጽ ላይ መተላለፍ /መውጣት አለበት።
2. ማህበሩ የጉባኤውን ጥሪ በኢሜል፤ በተንቀሳቃሽ ስልክ በሚላክ አጭር የጽሁፍ መልዕክት፤ በደብዳቤ ወይም ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያስተላልፍ ይችላል።
3. ማህበሩ አስፈላጊ ሆኖ ከአገኘው የጥሪ ማስታወቂያውን በመገናኛ ብዙኃን ሊያደርገው ይችላል።

አንቀጽ 21 ምልዓተ ጉባኤ ባለመገኘቱ የሚጠራ መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ

አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ባለመገኘቱ የተነሳ ሥራውን ማካሔድ ካልቻለ ለመጀመሪያው ጉባኤ በተደረገው ዓይነት ሁለተኛ ስብሰባ ይጠራል፡፡

አንቀጽ 22 ምልዓተ ጉባኤ ባለመገኘቱ የተነሳ የሚጠራ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

ምልዓተ ጉባዔ ባለመሟላቱ አስቸኳይ ጉባኤ ሳይሰበሰብ የቀረ እንደሆነ ሁለተኛ እና ካስፈለገም ሦስተኛ ስብሰባ ጥሪዎች በመጀመሪያውና በሚቀጥለው መሐል በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 366 እና 367 ድንጋጌዎች መሠረት መጠራት አለበት፡፡

አንቀጽ 23 ጉባኤዎችን በውክልና መሳተፍ

1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ጠቅላላ ጉባኤውን በወኪል አማካኝነት መሳተፍ ይችላል፤ ሆኖም ማንኛውም ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን ወኪል ሆኖ የሚሰጠው ድምጽ መጠን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡ ባለአክሲዮኑ በጉባኤው ላይ ወኪል እንዲገኝ ካደረገ እራሱ ለመሳተፍና ድምጽ ለመስጠት አይችልም፡፡
2. የውክልና ስልጣን ቅጽ ይዘትና ውክልናው የሚቀመጥበት ጊዜና ቦታ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፡፡ ሆኖም የውክልናው ቅፅ በወካዮች ተሞልቶ የሚቀመጥበት የጊዜ ገደብ ጉባኤው ከሚካሔድበት ጊዜ ከሶስት ቀን በፊት መጠናቀቅ አይችልም፡፡
3. አንድ ባለአክስዮን በአንድ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ተወካይ የሚመድበው በጽሁፍ በተዘጋጀ ሠነድ ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ 24 የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ

1. በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ በጉባኤው ላይ የተገኙ ባለአክስዮኖችን የሚያስረዳ የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ መኖር አለበት፡፡ ዝርዝሩ በስብሰባው የተገኙትን ባለአክስዮኖች ወይም በእንደራሴ የተወከሉት ባለአክስዮኖች ስምና አድራሻቸውን እና እያንዳንዱ ባለአክስዮን በማህበሩ ውስጥ ያለውን የአክስዮን መጠንና የሚሰጠውን የድምፅ ቁጥር ማሳየት አለበት፡፡
2. በጉባኤው ላይ የተገኙት ባለአክስዮኖች የተመዘገቡበት የተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በጉባኤው በተገኙት ባለአክስዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው የተፈረመበትና ስለመሆኑ በማህበሩ ፀሐፊ መረጋገጥ አለበት፡፡

አንቀጽ 25 የጥቅም ግጭት

1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ስለራሱ ወይም ሦስተኛ ወገንን ወክሎ ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡

2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የራሳቸውን ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም በማህበሩና በራሳቸው ጥቅም መካካል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግጭት በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ መስጠት አይችሉም፡፡
3. ምልዓተ ጉባኤ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 እና 2 ድምጽ የመስጠት መብት የተከለከሉ አክሲዮኖች ከቁጥር ውስጥ ይገባሉ፡፡
4. በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ፤ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው በባለክሲዮኖች ጉባኤ ድምጽ በነፃነት የመስጠት የባለአክሲዮኖች መብት አይገደብም፡፡

<u>አንቀጽ 26 ቃለጉባኤ</u>

1. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለ ጉባኤ ይመዘገባሉ፡፡ በቃለ ጉባኤ መዝገብ ላይ ተጽፈው በጉባኤው ላይ የተገኙት የዳይሬክተሮች አባላትና የማህበሩ ጸሃፊ ይፈርሙበታል፡፡ በዚህ ሁኔታ በመዝገቡ ላይ የተጻፈው ትክክል ስለመሆኑ በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሁለት ዳይሬክተሮች የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
2. ቃለጉባኤዎች ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት/መያዝ/ አለባቸው፡፡

ሀ. የጉባኤውን ጥሪ አደራረግ

ለ. ስብሰባው የተደረገበት ቦታና ቀን

ሐ. አጀንዳዎቹን

መ. በጉባኤው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም

ሠ. በስብሰባው ላይ የተገኙ አክስዮኖችን ብዛትና የምልዓተ ጉባኤውን ቁጥር

ረ. ለጉባኤው የቀረቡትን ሰነዶች

ሰ. የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ

ሸ. የተሰጡትን ድምፆች ውጤት እና

ቀ. ጉባኤው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች

3. ምልዓተ ጉባኤ ሳይገኝ ሲቀር ሰብሳቢው ይህንኑ በቃለ ጉባኤው መዝገብ ላይ ያሰፍራል፡፡
4. የቃለ ጉባኤዎች ቅጅዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሁለት ዳይሬክተሮች ይረጋገጣሉ፡፡

ምዕራፍ አምስት
የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን

<u>አንቀጽ 27 የዳይሬክተሮች ስያሜ</u>

1. ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጡ **አሥራ አንድ** አባላት ባሉት አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለመሆን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ የእድሜ፣ የትምህርት፣ የስራ ልምድ፣ የስነምግባርና ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ከተመረጡበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ የሥራ ጊዜውን የጨረሰ ዳይሬክተር ለሁለተኛ ጊዜ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ሰው በራሱም ሆነ በውክልና ከስድስት ተከታታይ አመታት በላይ በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችልም፡፡ ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤው የስራው ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሶስተኛ ያልበለጡትን ለሶስተኛ ዙር በቦርድ አባልነት እንዲሰሩ ሊመርጣቸው ይችላል፡፡
5. ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ይመርጣል፤ እንደዚሁም ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑስ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡
6. በማንኛውም ምክንያት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከተጓደለ እና የቀሩት አባላት 50% ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የተጓደሉትን ዳይሬክተሮች የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ባገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት በመተካት ለመሾም ይችላሉ፡፡ የምትክ ዳይሬክተሮች ሹመት እንዲጸድቅ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. የተተኩት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሹመት እንዲፀድቅ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤውም ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን ሊሾም ይችላል፡፡ ሹመታቸው በጠቅላላ ጉባኤው ሳይፀድቅ ቢቀር እንኳን በሹመታቸው ጊዜ ያከናወኑት ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

8. በማናቸውም ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከስድስት በታች ከሆነ አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ እንዲካሔድ ቦርዱ በ30 ቀናት ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት።

አንቀጽ 28 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የማህበሩን ስራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል።
2. ማህበሩ ጤናማ የፋይናንስ አስተዳደር፣ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈጸም አቅም ያለው መሆኑን ያረጋግጣል።
3. ባንኩ የሚያደርገውን ኢንቨስትመንት ያጸድቃል።
4. ትርፋማ በሆኑ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ባንኩ አክስዮኖችን እንዲገዛ፤ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ያለውን አክስዮን እንዲሸጥ፤ እንዲሁም አዲስ አክስዮን ማህበራትን ከሌሎች ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር በመሆን እንዲያቋቁም ይወስናል።
5. የባንኩን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።
6. የባንኩን መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰራተኞች ደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም ያጸድቃል።
7. የባንኩን ፖሊሲዎች ያጸድቃል፤ ያሻሽላል።
8. የባንኩ የወለድ ምጣኔ ፖሊሲና ተመን ያፀድቃል፤ ያሻሽላል።
9. የባንኩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል። በየበጀት ዓመቱ የሚከፈቱ የቅርንጫፎችን ቁጥር ይወስናል።
10. የባንኩን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሾማል፤ ከስራ ያሰናብታል።
11. የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና/ወይም የቦርድ የጥቆማ(እጩ አቅራቢ) እና ክፍያ ጉዳዮች ኮሚቴ Nomination and Remuneration Committee) በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት የባንኩን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ/ዎች እንዲሁም የማህበሩን ፀሐፊ ሹመት፤ ምደባና ስንብት ያፀድቃል።

12. የቦርድ የጥቆማ(እጩ አቅራቢ) እና ክፍያ ጉዳዮች ኮሚቴ (Nomination and Remuneration Committee) አቅራቢነት ቺፍ የውስጥ ኦዲተር፤ ቺፍ የሪስክ ኦፊሰርና ቺፍ ኮምፕሊያንስ ኦፊሰር ሹመትና ስንብት ያጸድቃል፡፡

13. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎች በወቅቱ በማከናወን የባንኩን የሂሳብ ሚዛን ትርፍና የኪሳራ ሂሳብ ያዘጋጃል፣

14. የማህበሩን የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ይጠራል፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጉባአው ያቀርባል፡፡

15. የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የአክሲዮን መዝገብ፣ የዳይሬክተሮች መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

16. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመትና የምርጫ አፈፃፀም ሥነሥርዓት ደንብ /መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

17. የባንኩ የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

18. ለባንኩ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሃገር ውስጥና ከውጭ ሃገር ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ለመበደር የሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ ያፀድቃል፡፡

19. የግዴታ ወረቀቶችን ያወጣል ከዚያም ጋር የተያያዙትን ዋስትናዎች ያፀድቃል፡፡

20. የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ባንኩ የሚንቀሳቀስ ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን እንዲገዛ፤ እንዲሸጥ፤ የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ እንዲከራይ ወይም እንዲያከራይ መወሰን ይችላል፡፡

21. ለባንኩ ስራ አላማዎች ግብ መምታት አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

22. ገንቢ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ሃሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

23. የማህበሩ ካፒታል እንዲጨምር ወይንም እንዲቀንስ ለጠቅላላ ጉባኤ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

24. ባንኩ በሚያዘጋጃቸው የውስጥ ደንብ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ከተሰጡት ገደቦች በላይ የሆኑ ግዥዎችን መርምሮ ያፀድቃል፡፡

25. በቅድሚያ በዝርዝር የተዘጋጀን ደንብ መሰረት በማድረግ በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞች ከረዥም ጊዜ አገልግሎት በኃላ ከሥራ ሲሰናበቱ ወይም የተለየ የሥራ አፈጻጸም ሲያስመዘግቡ ስጦታ በአይነት ወይም በገንዘብ መሸለም ይችላል፡፡

26. የአገሪቱን ሕግ መሰረት በማድረግ ማህበሩ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል በበጎ አድራጎት ተግባር ለተሰማሩ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ወይም ለፌዴራል ወይም ክልላዊ መንግስት የአይነት ወይም የገንዘብ ስጦታ ለማድረግ ይችላል፡፡
27. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት ተብለው የተዘረዘሩ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
28. በሕግ ፤ በዚህ የመመስረቻ ሰነድ ወይም በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤዎች ለማህበሩ ሌላ አካል /ሌሎች አካሎች/ በተለይ ከተሰጡ ሥልጣኖች በስተቀር ፤ የማህበሩ ድርጅታዊና ሥልጣኖች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ናቸው፡፡
29. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰኑ ስልጣኖቹን በዝርዝርና ግልጽ በሆነ መልኩ ለባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 29 የዋስትና አክስዮኖች

1. የብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆነው የሚመረጡ ሰዎች የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና እንዲያሲዙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የኩባንያው ባለአክስዮኖች በሚያደርጉት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አማካኝነት ይህንን የመመስረቻ ጽሁፍ በማሻሻል ዳይሬክተሮች የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና እንዲያሲዙ ለመወሰን ይችላሉ፡፡
2. የብርሃን ባንክ አ.ማ. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 29(1) ወይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 302 መሰረት በመመስረቻ ጽሁፉ ላይ ስለመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ውሳኔ እስከሚያስተላልፍበት ጊዜ ድረስ በሥራ ላይ ያሉ የኩባንያው ዳይሬክተሮች ሥራቸውንና ተግባሮቻቸውን በትክክልና በሚገባው አሠራር ለመወጣታቸው ዋስትና እንዲሆን እያንዳንዳቸው 50/ሃምሳ/ የተመዘገቡ አክስዮኖች በማህበሩ ዘንድ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡ እነዚህ አክስዮኖች ባለቤቶቹ ዳይሬክተርነታቸውን እስካለቀቁና ለማህበሩ ያለባቸውን ኃላፊነት በሙሉ እስካልተወጡ ድረስ አይለቀቁም፡፡

አንቀጽ 30፡ የዳሬክተሮች ቦርድ ስብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ የቦርዱ አባላት በሙሉ በተገኙበት ስብሰባ ከአባላቱ መካከል በአብላጫ ድምጽ ይመረጣሉ፡፡
2. የቦርድና የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም እርሱ/እርሷ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢ ወይም እርሱ/እርሷ በማይኖርበት/በማትኖርበት

ጊዜ በሥራ ቀደምትነት ባለው ዳይሬክተር ሁለቱም ከሌሉ በስብሰባውበሚሾመው ዳይሬክተር ይመራሉ።

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው/ዋ/ በሚመርጡት ቦታ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለባንኩ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም እንደአስፈላጊነቱ ብዛት ይሰበሰባል። ሆኖም በተለያየ ምክንያት ቦርዱ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ማድረግ የማይችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ማድረግ አለበት።

አንቀጽ 31 የዳይሬክተሮች /የቦርድ አባላት/ ግዴታ፤ ተግባርና ኃላፊነት

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማህበሩን የበለጠ ስኬታማ ያደርጋል ብለው በቅን ልቦና ያመኑበትን እርምጃ መውሰድ አለባቸው። የመላው ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሥራት ይኖርባቸዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 31(1) ሥር የተመለከተውን ኃላፊነት በሚወጣበት ጊዜ አንድ ዳይሬክተር የማህበሩን የረጅም ጊዜ ጥቅም፣ የሠራተኞች ጥቅም፣ ከማህበሩ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸውን ሰዎች ጥቅም፣ የማህበሩ ሥራ በማህበረሰቡ እና በአካባቢው ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኃላፊነቱን በጥንቃቄ፣ በብልሀትና በትጋት መወጣት አለበት። በጥንቃቄ ወይም በትጋት ጉድለት በማህበሩ እና በባለአክሲዮኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ዳይሬክተሩ ተጠያቂ ይሆናል።
4. ጠቅላላ ጉባዔው ካልፈቀደ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በራሳቸው ወይም በሦስተኛ ወገኖች ስም ከማህበሩ ጋር መወዳደር ወይም ተወዳዳሪ በሆኑ የንግድ ማህበራት ውስጥ አባል መሆን አይችሉም።
5. የአንድ ማህበር ዳይሬክተር ከሚመራው ማህበር ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ራሱን ማራቅ አለበት።
6. እያንዳንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በራሱ እና በማህበሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችልን ማንኛውንም ሁኔታ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

7. በተለይም ከማህበሩ ጋር ሊደረግ የታሰበ ወይም የተደረገ ውል ወይም ሌላ ዓይነት ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የቦርድ አባሉን ጥቅም የሚነካ ከሆነ አባሉ ስለጥቅሙ ባሕሪ እና መጠን ለተቀሩት ዳይሬክተሮች የተሟላ መግለጫ መስጠት አለበት።
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 31(6) እና 31(7) ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም መግለጫ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ስለመኖሩ እንደታወቀ ወዲያውኑ መቅረብ ይኖርበታል።
9. አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ በሦስተኛ ወገን ስጦታም ሆነ ሌላ ዓይነት ጥቅም የተሰጠው እንደሆነ የጥቅሙ ተጋሪ ያልሆኑ ዳይሬክተሮችን ወይም የማህበሩን ጠቅላላ ጉባዔ ሳያስፈቅድ መቀበል አይችልም።

<u>አንቀጽ 32 ፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ</u>

1. ከግማሽ በላይ ዳይሬክተሮች በስብሰባው ካልተገኙ ወይም ካልተወከሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም።
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚተላለፈው በተቻለ መጠን በሙሉ ድምፅ ይህም ካልሆነም በድምጽ ብልጫ *ነው። ድምጽ እኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የሚደግፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል።*
3. ማናቸውም ዳይሬክተር አንድ ድምጽ የመስጠት መብት አለው።
4. በቦርድ ስብሰባ ያልተገኘ ዳይሬክተር የሚወክለው ሌላ ዳይሬክተር ሊሰይም ይችላል፤ ሆኖም አንድ ዳይሬክተር ከአንድ ውክልና በላይ መቀበል አይችልም።
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን ለማድረግ አጋዥነቱ አስፈላጊ ነው ብሎ በገመተ ጊዜ ሁሉ በባለሙያዎች ምክር ሊረዳ ይችላል።
6. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው በተገኙ አባላትና በማህበሩ ጸሃፊ መፈረም አለባቸው። ቃለ-ጉባኤው በቃለ-ጉባኤ መዝገብ መያዝ አለበት።የውሳኔዎች ቅጅዎች በሙሉ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይፈረማሉ።
7. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መምሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ በቪዲዮ ኮንፈረስ/በዙም/ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ መሳተፍ ይችላሉ።

8. የመገናኛ ዘዴው የተሰብሳቢዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል እንዲሁም ውጤታማ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። የመገናኛ ዘዴው ቢያንስ የተሳታፊዎችን ድምጽ ሳይቆራረጥ የሚያስተላልፍ እና ተሰብሳቢዎቹን በአንድ ጊዜ መሳተፍ እንዲችሉ የሚፈቅድ መሆን አለበት።
9. በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሳተፉት የቦርድ አባላት ድምጻቸውን በቃል መስጠት ይችላሉ።
10. ከቦርዱ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ቢያንስ **1/3ኛ(አራት አባላት)** በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በስተቀር በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 32(7-9)መሰረት በተደረገ ሰብሰባ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም።

<u>አንቀጽ 33 ፡ የዳይሬክተሮች አበልና የሥራ ዋጋ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእያንዳንዱ ዳይሬክተር የሚከፈለው ማናቸውም አበል ወይም ጥቅም በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

አንቀጽ 34፡ <u>ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ</u>

1. ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የኦዲተሮችን እና የማህበሩን ፀሐፊ እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 306(6)(ለ)(ሐ)(ረ) የተጠቀሱ ሰዎች የግል ሁኔታ፣ ሙያቸውን፣ በሌሎች የንግድ ማህበራት ወይም ድርጅቶች ውስጥ ያላቸውን ጥቅም፣ ስራ፣ የቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በዝርዝር የሚያሳይ መዝገብ በዋና መሥሪያ ቤት ይይዛል።
2. የቦርድ ዳይሬክተሩ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስምና የዋና መስሪያ ቤቱን አድራሻ በመዝገቡ ይካተታል።
3. ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል ማናቸውም በተመለከተ በመዝገቡ የሰፈሩ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ካለ ይህንኑ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለባንኩ ዋና ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት።

አንቀጽ 35 ከዳይሬክተርነት ስለመነሳት

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013፤ በባንክ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 592/2000 ከአንቀጽ 15-17፤ በባንክ ሥራ/ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 1159/2011፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ልዩ ልዩ

መመሪያዎች፤ እንዲሁም በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም ሌሎች ሕጋዊ ሰነዶች ላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከአባልነት ሊነሳ/ሊወገድ ይችላል፡፡

ሀ. በጠቅላላ ጉባኤ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውሳኔ
ለ. ዕምነት በማጉዳል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተላለፈበት
ሐ. አንድ ዳይሬክተር ለሥራው ተገቢ ላለመሆኑ በቂ ምክነያት ሲኖር፤ ይኸውም የባንኩን ሥምና ጥቅም በሚጎዳ ተግባር መሰማራቱ በተቀሩት ዳይሬክተሮች ታምኖበት በዳይሬክተሮች የሥራ ባልደረቦቹ/ቿ በሙሉ ሥራውን እንዲለቅ/ እንድትለቅ/ በጽሁፍ ሲጠየቅ/ስትጠየቅ/
መ.. ዳይሬክተሩ ከዓቅም በላይ የሆነ ጉዳይ እንዳጋጠመው በመግለጽ የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ፣
ሠ. ሲከስር ወይም ዕዳ መሸፈን ሲሳነው ወይንም ዕዳውን አለመክፈሉ አንዳይታወቅ ከአበዳሪዎቹ/ቿ ጋር ከተመሳጠረ/ች
ረ. በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ቦርዱ ከሚያደርጋቸው ስብሰባዎች መካከል ቢያንስ 75% በአካል ለመገኘት ያልቻለ የቦርድ አባል በጠቅላላ ጉባኤው ተቀባይነት ያለው በቂ ምክንያት ካላቀረበ በስተቀር ወዲያውኑ ከቦርድ አባልነት ይወገዳል፡፡
ሸ. ዳይሬክተሩ ሥልጣኑን ከማህበሩ ጥቅም ጋር በሚጋጭ አኳኋን በመገልገል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያልተገባ ጥቅም ማግኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 297/2/ መሰረት ከዳይሬክተርነት መውረድ አለበት፡፡

ምዕራፍ ስድስት
የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ኃላፊነት

አንቀጽ 36 የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት

ባንኩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይኖረዋል፡፡ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 37 የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የባንኩን መደበኛ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ሙሉ የሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን አለው፡፡ ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሟላት ባንኩን ወክሎ በባንኩ ስም ይሰራል፡፡
2. ባንኩ በዓለም ዓቀፍና በአገር ውስጥ በሚኖሩት እንቅስቃሴዎች ከሦስተኛ ወገን ጋር ለሚሰሩና በመንግስታዊና በግል ድርጅቶች ሁሉ ፊት እንዲሁም በባንኮች ወይም በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ባንኩን ይወክላል፡፡

3. የባንኩን ደንቦችና የሥነሥርዓት ሕግጋትን አርቅቆ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያጸድቃቸው ያቀርባል፡፡
4. የባንኩን የሒሳብ አያያዝ ይመራል፡፡ ይቆጣጠራል፡፡
5. የባንኩን የዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡ ለዚህም የስራ አመራር ስብሰባዎችን ይጠራል፡፡
6. ሕግና ይህ መመስረቻ ጽሁፍ በደነገጉት መሰረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ሒሳቦች ያቋቁማል፡፡
7. በባንኩ ስም በሌላ ባንክ ወይም ባንኮች የባንክ ሒሳብ ይከፍታል፡፡ ያንቀሳቅሳል፡፡ የተከፈቱትን ሒሳቦች በየሩብ ዓመቱ ለቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
8. የሐዋላ ቼኮችን፤ የሒሳብ ሰነዶችን የምንዛሪ ሰነዶችን የተስፋ ሰነዶችን ሌሎች የስምምነት ሰነዶችንና እንዲሁም የገቢና የወጪ ሰነዶችን ይፈርማል፤ ይቀበላል፤ ወጪ ያደርጋል፤ ያዘጋጃል፤ ሥራ ላይ ያውላል፤ያፀድቃል፤ ቅናሽ ያደርጋል፡፡
9. የዕርጅና ቅናሽ ተመን ይመድባል፡፡ እንዲሁም ቦርዱን በማሳወቅ ባንኩን ከኪሣራ ፤ ከጥፋት፤ ከድንገተኛ አደጋ ከማንኛውም ተጠያቂነት ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከማንኛውም የመድን ኩባንያ ጋር ተፈራርሞ ያስገባል፡፡
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወስነውና በባንኩ ዓላማዎች ክልል መሰረት የባንኩን ገንዘብ በሥራ ላይ ያውላል፡፡ በቦርዱ ሲፈቀድ አዋጪ ከሆኑ አክስዮን ማህበራት አክስዮን ይገዛል ወይም ይሸጣል፡፡ አክስዮን ማህበራትን ያቋቁሟል፡፡
11. የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት ለመግዛት፤ ለመሸጥ ፤ ለመከራየትና ለማከራየት የሚያስችሉ ውሎችን ባባንኩ ስም መዋዋል ይችላል፡፡
12. ለባንኩ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ሦስተኛ ወገኖችን ወይም የባንኩን ሠራተኞች መወከል ይችላል፡፡
13. ባንኩን ወክለው መክሰስ ወይም መከራከርና መልስ መስጠት፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ባለሙያ/ጠበቃ/ነገረ ፈጅ/ መወከል ይችላል፡፡
14. የባንኩን ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፡፡
15. የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅር ያዘጋጃል፤ በቦርድ ሲጸድቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡
16. በፀደቀው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎችየባንኩን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፡፡ ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን ለዳይሬክተሮች ቦርድ በማቅረብ ያስወስናል፡፡
17. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ከውስጥ ኦዲት፤ ከሪስክ ማኔጅመንትና ኮምፕሊያንስ የሥራ ኃላፊዎች ውጭ ያሉትን ሁሉንም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች በመምረጥ ቦርዱ እንዲያጸድቃቸው ያቀርባል፡፡
18. የባንኩ የወለድ ምጣኔ ፖሊሲ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፡፡

19. የውጭ ምንዛሪ ተመንን አስመልክቶ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፡፡ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፡፡

20. የባንኩ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ያጸድቃል፡፡

21. ለባንኩ ስራ አስፈላጊና አስተማማኝ የሆነ የኢንፎርሜሽ ሲስተም በማዘጋጀት እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፡፡

22. ለባንኩ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአገር ውስጥ ባንኮችና ሌሎች የፋናንስ ተቋማት ገንዘብ ይበደራል፡፡ በባንኩ ስም የብድርና የመያዣ ውሎችን ይፈራረማል፡፡

23. ባንኩ ከፎርክሎዠር ጋር በተያያዘ የተረከባቸውን ንብረቶች፣ ጉዳት የደረሰባቸው ወይም በእርጅና ምክንያት መወገድ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶች እና ከባንኩ መደበኛ ስራ ጋር በተገናኘ ሌሎች የባንኩ የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በባንኩ መመሪያ መሰረት እንዲሸጡ ይወስናል፡፡

24. በመመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ ያቀርባል፣

25. በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ወይም በሕግ ተለይተው የተሰጡ ሌሎች ስራዎች ያከናውናል፣

26. ዋና ሥራ አስፈጻሚው በተለይ የሚከተሉትን በሚመለከት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት አለበት፡፡

    ሀ. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎች በወቅቱ በማጠናቀቅ የባንኩን የሒሳብ ሚዛን እና የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ ማዘጋጀት፤

    ለ. ተገምጋሚ የሚሆነውን ያለፈውን የባንኩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ማርቀቅ፤

    ሐ. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ደንብ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ ማቅረብ፤

    መ. ለቦርዱ ስብሰባዎች ከቦርዱ ሰብሳቢና የማህበሩ ጸሃፊ ጋር በመመካከር አጀንዳ ማዘጋጀት፤

    ሠ. ለባንኩ ሥራ ፤ ማስተዋወቂያ በሂደቱም አስፈላጊ ለሆኑ ልዩ ልዩ ሕጋዊ ወጪዎች ሁሉ ክፍያ ማድረግ፤

    ረ. በአጠቃላይ በዚህ ሰነድ በተለይ ያልተጠቀሱም ቢሆን ለባንኩ ሥራና ለዓላማዎቹ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች ማከናወን፤

    ሰ. ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የዳይሬክተሮችን ቦርድ ስብሰባዎች ማዘጋጀት እና ማቀናበር፤

    ሸ. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ተብለው የተመደቡ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>ስለ የማህበር ጸሃፊ</u>

አንቀጽ 38፡ <u>የማህበሩ ፀሐፊ</u>

1. የማህበሩ ፀሐፊ በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡
2. የፀሐፊው ተጠሪነት ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 39 የማህበሩ ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የማህበሩ ጸሃፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አሉት፡፡

1. የማህበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ ፤
2. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፤
3. ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤
4. የባለአክስዮኖችንና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤
5. ቃለ ጉባዔዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤
6. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ ለማህበሩ ጸሃፊ የተሰጡ ተግባራትን ማከናወን፤
7. በበዋና ሥራ አስፈጻሚው እና በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

ምዕራፍ ስምንት

የማህበሩ ኦዲተሮች(ተቆጣጣሪዎች)

አንቀጽ 40፡ <u>የማህበሩ ኦዲተሮች</u>

1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸው ገለልተኛ የውጭ ኦዲተሮች በማህበሩ   ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ፡፡
2. ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ ሃያ በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች እራሳቸው የመረጡትን የውጭ ኦዲተር መሾም ይችላሉ፡፡

3. የኦዲተሮች የስራ ዘመን የሶስት በጀት አመት ሒሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ድረስ ይሆናል፡፡
4. የኦዲተሮች የስራ ዋጋ ክፍያ በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡
5. የኦዲተሮች የስራ ዋጋ ክፍያ በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡
6. ኦዲተሮች በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በባንኩ የሥራ ቦታዎች በመገኘት ማናቸውንም የምርመራና የቁጥጥር ሥራ ያደርጋሉ፡፡ ለምርመራ ሥራቸው አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑበትን ውሎችን፤ ስምምነቶችን፤ የሒሳብ መዛግብትንና ቃለጉባኤዎችን በአጠቃላይ የባንኩን እንቅስቃሴዎች ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን ሁሉ እንዲቀርቡላቸው በመጠየቅ ምርመራ ያከናውናሉ፡፡
7. ማናቸውም አይነት የባለአክስዮኖች ጉባኤ ሲደረግ ኦዲተሮች መገኘት አለባቸው፡፡
8. ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ተገቢውን አስተያየት ይሰጣል፡፡
9. የማህበሩ ሒሳቦች ሲቀርቡለት ጉባኤው ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
10. ለባለአክስዮኖች እንዲከፋፈል ስለቀረበው የትርፍ ድርሻ አስተያየት ያቀርባል፡፡
11. የማህበሩን ሒሳቦች በሚመረምርበትና በሚቆጣጠርበት ወቅት ያጋጠመውን ሕገ ወጥ የሆኑ ተግባራት ለዳይሬክተሮች ቦርዱና ለባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያስታውቃል፡፡
12. የኦዲተሮች ተግባርና ሃላፊነት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 348 – 354፣ በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ
የማህበሩ ሒሳብ

<u>አንቀጽ 41 ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የሒሳብና የመዛግብት አያያዝን በተመለከተ የደነገጉዋቸው በማህበሩ ሒሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተፈጻሚ ናቸው፡፡

<u>አንቀጽ 42 ሒሳብና ዓመታዊ ሪፖርት ዘገባ</u>

1. የባንኩ የበጀት ዓመት እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ያበቃል፡፡
2. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ማብቂያና ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 28(13) መሰረት ለሚቀርበው ሪፖርት /ዘገባ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሀ. ዝርዝር የንብረት ቆጠራና የንብረትና የዕዳ ግምት ያዘጋጃል፡፡

ለ. እንደዚሁም ያለፈውን የበጀት ዓመት የሒሳብ ሚዛን እና የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ መግለጫ፤ በተጨማሪም ባንኩ ባለፈው የበጀት ዓመት ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎችና የነበሩት ጉዳዮች የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያሳይ ዘገባ ያዘጋጃል።

ሐ. ዘገባው ስለትርፍና ኪሳራ ሒሳብ እና ስለኦዲተሮች ክፍያ(የሥራ ዋጋ) ዝርዝር መረጃና እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዓመታዊ ትርፍ አደላደል ሃሳቦችን ማቅረብ አለበት።

አንቀጽ 43 ሒሳቦችንና ሪፖርት(ዘገባ) ለኦዲተሮች ማቅረብ

የንብረት ቆጠራ የሒሳብ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት(ዘገባ) ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪው ከመላኩ ቢያንስ ከ40 ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች መቅረብ አለባቸው።

አንቀጽ 44 የሒሳብ ሚዛንና የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ መግለጫ ማዘጋጀት

የሒሳብ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሒሳብ መግለጫና እንዲሁም የዕዳ ክፍያና የእርጅና የዋጋ ቅነሳ ሒሳቦች መግለጫ አዘገጃጀት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና የባንክ ሥራ ፈቃድና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 592/2008(በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) ድንጋጌዎችንና በየጊዜው ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

ምዕራፍ አስር

ተፈላጊ ዋና ገንዘብ (ካፒታልና) መጠባበቂያ ሒሳብ ስለመያዝ

አንቀጽ 45 ተፈላጊ ዋና ገንዘብ ስለመያዝ

1. ማህበሩ በማናቸውም ጊዜ ፡-

ሀ. ሕጋዊ መጠባበቂያ ሒሳብ ይኖረዋል። ይህም ዓመታዊ የትርፍ ክፍያ ድርሻ ከመገለፁ አስቀድሞ ከዓመቱ ትርፍ ላይ ታክስ ተነስቶለት ከሚቀረው የተጣራ ትርፍ ላይ ሃያ አምስት በመቶ(25%)ያላነሰ ገንዘብ በመቀነስ የሚጠራቀም ነው። ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፍ ባንኩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚይዘው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንዲሆን ያደርጋል።

ለ. ያልተከፋፈለ ትርፍ የተያዘና ሌሎች መጠባበቂያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል።

2. የባንኩን ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ ከፍ ለማድረግ ዓላማ ሲባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቅነሳውን ዝርዝር ሁኔታዎች አስመልክቶ አስቀድሞ በሚሰጠው ፈቃድና መመሪያ መሰረት የማህበሩን ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ መቀነስ ይቻላል፡፡

አንቀጽ 46 በጥሬ ገንዘብ ተለዋጭ የሚሆን አነስተኛ ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሚዛን

ባንኩ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚወስነው ልክ በጠቅላላ ያለበት የተቀማጭ ገንዘብ ዕዳ በመቶኛ የሚሆን የመጠባበቂያ ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ ዘንድ ያኖራል፡፡

አንቀጽ 47 ልዩ መጠባበቂያ ገንዘብ

ባንኩ፡-

1. በዳይሬክተሮች፤ በዋና ሥራ አስፈጻሚ/ በምክትል ሥራ አስፈጻሚዎች ፤ በመምሪያ ኃላፊ ወይም በማንኛውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ቸልተኝነት ወይንም ዕምነት ማጉደል ለሚደርስ ኪሳራ መሸፈኛ የሚሆን ልዩ መጠባበቂያ ገንዘብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት መጠን ይይዛል፡፡
2. ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሳራ ለመዳን ሲባል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደዚህ ዓይነት ከመሰለ ኪሳራ የሚያድን ዋስትና በመስጠት ሥራ ላይ ከተሰማራ የመድህን ድርጅት ዋስትና ይገባል፡፡

አንቀጽ 48 መጠባበቂያዎች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 47 ከተደነገገው በተጨማሪ ማህበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚጠብቀውን ለማሟላት በሚያስችለው መጠን ለሚከተሉት የሚውሉ መጠባበቂያዎች ይይዛል፡፡

1. ቢያንስ በዓመት የሚሰላ ሆኖ የአገልግሎት ዘመንን መሰረት ያደረገ የንብረት የእርጅና ዋጋ ቅነሳን፤ የተከማቸ የእርጅና ዋጋ ቅነሳንና ያልተከፈሉ ወይም ያልተሰረዙ ወይም አጠራጣሪ ዕዳዎችን ጨምሮ ለመሸፈን የሚሆን፤
2. ሥራ ለሚካሔድበትና ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ፤
3. ከማደራጀት ወይም የንግድ ሥራ ሽያጭን ወይም የባንኩን መልካም ስም ከማስፋፋት ከማቋቋሚያ ኮሚሽንና የአክስዮኖችን ዋስትና ጭምር ለመክፈያ፤
4. በማናቸውም ሕግ መሰረት የተገቡ ግዴታዎችን በዋስትና ወይም በመያዣ ለማረጋገጥ የተሰጡ ንብረቶቹን ዋጋ ለመሸፈን የሚውል ሂሳብ፤ ይህ የሚደረገው ግን ግዴታዎቹ (ተዘማጅነት ያላቸው ግዴታዎች ጭምር) ባንኩ ስለካፒታልና ስለመጠባበቂያ ገንዘብ የሚፈለጉበትን ሕጋዊ መለኪያዎች ማሟላቱን ለማረጋገጥ ሲባል ከተደረገው ስሌት ውስጥ ያልተቃለሉ ከሆኑ እና የንብረቶቹም

በዋስትና ወይም በመያዣነት መሰጠት ባንኩ ሊያገኛቸው የማይችልበትን ውጤት አስከትሎበት የሕዝብ ዕዳዎቹን እንዳይወጣ የሚያደርገው ሲሆን ነው።

5. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪዎች ለሚገለጹ ጉዳዮች ወጪ መሸፈኛ።

አንቀጽ 49 የሒሳብ ሚዛን መግለጫዎችን ስለመላክ

1. ማህበሩ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ አንድ ቅጅ እንዲሁም ጉባኤው መግለጫውን ያጸደቀበት ውሳኔ ቃለጉባኤ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫው በጸደቀ በ30 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የመንግስት አካል መላክ አለበት።
2. ማህበሩ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች ሪፖርቶችን፣ ለባለአክስዮኖች የሚያቀርበውን ሪፖርት ትክክለኛ ቅጂ፣ እንዲሁም የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ቃለጉባኤ ትክክለኛ ቅጂ በ20 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት።

ምዕራፍ አሥራ አንድ
መፍረስና ሒሳብ መጣራት

አንቀጽ 50 ለማህበሩ መፍረስ የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008(በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተመለከቱት ስለኩባንያዎች መፍረስና ሒሳብ ማጣራት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በባንኩ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. ከላይ የተጠቀሰው ባንኩን የማፍረስና ሒሳብ የማጣራት ሥልጣንና ተግባር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተደነገገው መሰረት ይከናወናል።
3. ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ለማህበሩ መፍረስና ሂሳብ መጣራት በቂ ይሆናል።

   ሀ. ማህበሩን የተቋቋመበትን ዓላማ ሲፈጽም ወይም ለመፈጸም ሳይችል ሲቀር፤

   ለ. ማህበርተኞች የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲስማሙና በቅድሚያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን በማስፈቀድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በፈቃደኝነት ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤

   ሐ. ማህበሩ የአስተዳደር አካላት የሌሉት በመሆኑ ምክንያት ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት የንግድ ማህበራትን የሚመዘግበው አካል ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፡

   መ. የባለአክስዮኖች ቁጥር በሕግ ከተፈቀደው በታች ሲሆን ፤

   ሠ. የማህበሩ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን ፤

   ረ. ማህበሩ የዋና ገንዘቡን ሦስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣና በዚሁ ምክንያት የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን።

   ሰ. ጥቅም አለኝ በሚል ሰው ጠያቂነት ማህበሩ እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ሲወሰን።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት
ልዩ ልዩ ደንቦች

አንቀጽ 51 በመመሥረቻ ሰነድ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች

1. በሕግ በሌላ ሁኔታ እስካልተወሰነ ድረስ የመመስረቻ ሰነዱ የሚሻሻለው በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
2. የመመስረቻ ሰነዱን ለማሻሻል ድምፅ እንዲሰጡ የተጠሩ አስቸኳይ ጉባኤዎች በዚህ መመስረቻ ሰነድ ድንጋጌዎች መሰረት የሥራቸውን አካሔድ መምራት አለባቸው፡፡

አንቀጽ 52 ካፒታልን ከፍ ማድረግ(ማሳደግ)

1. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሳይፈቅድ የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ አይቻልም፡፡
2. በባለአክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው በሚደረግ ውሳኔ አዳዲስ ልዩ ቅድሚያ መብት የሚያሰጡ አክስዮኖችን በመፍጠር የባንኩን ካፒታል ማሳደግ ይቻላል፡፡
3. የአክስዮኖች ሽያጭ መክፈቻ ቀን ይፋ ከመሆኑ ከ10 ቀናት በፊት በጋዜጣ ላይ በሚደረግ የአክስዮን ሽያጭ ማስታወቂያ አማካኝነት ለባለአክስዮኖች ከ30 ቀናት ባላነሰ ጊዜ አክስዮን እንዲገዙ የሚገልጽ ጥሪ ይከናወናል/ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በባንኩ ዋና መ/ቤት ውስጥ በሚገኝ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦታ እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡ ባንኩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የጥሪ ማስታወቂያውን በመገናኛ ብዙኃን ሊያርገው ይችላል፡፡
4. አዲስ አክስዮኖችን ለማግኘት(ለመግዛት) ለመመዝገብ ለባንኩ በሚቀርብ ማመልከቻ ከምዝገባው በፊት መከፈል ያለበትን ገንዘብ አብሮተ ካልተላከ በቀር ውጤት የለውም፡፡
5. የማህበሩ ዋና ገንዘብ አዲስ አክስዮኖችን በማውጣት ወይም የነባር አክስዮኖችን ዋጋ በመጨመር ማሳደግ ይቻላል፡፡
6. የአዲስ አክስዮኖች ዋጋ በሚከተሉት መንገዶች ሊከፈል ይችላል፡፡
   ሀ. በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት፤
   ለ. ማህበሩ ያሉበትን የመክፈያ ጊዜያቸው የደረሰ ዕዳዎች በአክስዮን በማቻቻል፤
   ሐ. መጠባበቂያ ወይም ማህበሩ ሊያዝባቸው የሚችሉ ሌሎች ገንዘቦችን ወደ ዋናው ገንዘብ በመጨመር፤
   መ. የዕዳ ሰነዶችን ወደ አክስዮን በመለወጥ፤
7. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ ዋና ገንዘብ እንዲያድግ የሚያሳልፈው ውሳኔ በአምስት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
8. የማህበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደጉ ሁኔት በንግድ ሕግ አንቀጽ 442-461 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይከናወናል፡፡

9. የማህበሩን ካፒታል በማህበሩ ተወካይ በተፈረመ መግለጫ አዲስ አክስዮኖችን ለሽያጭ ለሕዝብ በማቅረብ ማሳደግ ይቻላል። የተባለው መግለጫ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 447 መሰረት ይዘጋጃል።

አንቀጽ 53 የተመዘገበውን የአክስዮኖች ግዥ መግለጽ

ዳይሬክተሮች የሚከተሉትን ነጥቦች ያቀፈ መዝገብ (ማስታወሻ) ይይዛሉ።

1. አዲስ አክስዮኖች በሙሉ የተገዙ መሆናቸውን፤
2. መከፈል ያለባቸው ሒሳቦች ተጠናቅቀው የተከፈሉ መሆናቸውን
3. የተፈቀደው የካፒታል ጭማሪ ተግባራዊ መሆኑን፤
4. በመመሥረቻ ሰነዱ ላይ የተደረጉት አስፈላጊ ማሻሻያዎች የተስተካከሉ መሆናቸውን።

አንቀጽ 54 በዓይነት መዋጮ የዋና ገንዘብ/ካፒታል/ መጨመር(ማሳደግ)

1. የማህበሩ ዋና ገንዘብ ለማሳደግ የዓይነት መዋጮ የሚከፈል ከሆነ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 260፣ 261 እና 262 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 55 የካፒታል መቀነስ

1. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር የማህበሩን ካፒታል መቀነስ አይቻልም።
2. የማህበሩ ዋና ገንዘብ ቅነሳ ከተደረገ በንግድ መዝገብ መመዝገብ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣና በማህበሩ ድረ-ገጽ መውጣት አለበት።
3. የማህበሩን ዋና ገንዘብ መቀነስ የሚቻለው፡-

3.1 በአክስዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመቀነስ ወይም

3.2 ነባር አክስዮኖችን አነስተኛ ቁጥር ባላቸው አዲስ አክስዮኖች በመለወጥ ነው።

3.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ሌላ መንገድ፤

4. ከካፒታል ቅነሳ ጋር የተያያዘ የጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔዎች የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት ይፈጸማሉ።

አንቀጽ 56 የሀብትና ዕዳ የሒሳብ መግለጫን በማስታወቂያ ስለማውጣት

1. የጸደቀው የማህበሩ የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ አንድ ቅጅ እንዲሁም ጉባኤው መግለጫውን ያጸደቀበት ውሳኔ ቃለጉባኤ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫው ከጸደቀ በኋላ በማህበሩ ድረ-ገጽ ላይ መውጣት አለበት።

2. ማህበሩ የሒሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የኦዲተሩን መግለጫ አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ጠቅላላ ጉባኤው በተከናወነ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ አሳትሞ ማውጣት አለበት፡፡

አንቀጽ 57 የማህበሩ መፍረስና ንብረት መጣራት

በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008(**በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው**)፤ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 49 መሰረት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 58 የማህበሩ የሥራ ዘመን/የተቋቋመበት ጊዜ

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

አንቀጽ 59፡ ተፈጻሚ ሕግ

1. ይህ መመስረቻ ጽሑፍ በባንክ ሥራ አዋጅ፣ ከኢትዮጵያ የንግድ ሕግና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ይፈጸማሉ፡፡
3. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጹት ጉዳዮች ሁሉ ለሴቶችም ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በባንኩ ውስጥ ባለአክስዮን፤ ዳይሬክተር፤ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤ ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤ የመምሪያ ወይም የዋና ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ለመሆን የሚያስፈልገውን መስፈርት እስካሟሉ ድረስ ሊከለከሉ አይችሉም፡፡

አንቀጽ 60፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የወጣው የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበሩት የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ ይጠናቀቃሉ፡፡

አንቀጽ 61 መመስረቻ ጽሁፉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመስረቻ ጽሁፍ በብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች ስድስተኛው አስቸኳይ ጉባኤ ዛሬ ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም. ጸድቋል:: በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ታይቶ ሲፈቀድና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አጀንሲ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና እና ተፈፃሚ ይሆናል፡፡